በስደት የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አባላት አስተባባሪ ኮሚቴ
Coordinating Committee of Exiled Members of Ethiopian Teachers' Association

የተሰጠ መግለጫ

ሕዳር 10 ቀን 2006 ዓ.ም

## "አያያዙን አይተው ጭብጠውን ቀሙት" ወይ ነዶ!!

ኢትዮጵያውያን አያት ቅድመ አያቶቻችን ከውጭ ወራሪዎችና ከውስጥ ቦርባሪዎች በመከላከል ክቡር ሕይወታቸውን ገብረው እኛ እንድንኮራባቸውና በክብርም እንድንኖር አድርገዋል። በእኛ ዘመን በታሪክ አጋጣሚ ከመሐላችን የበቀሉ አሜኬላዎች ለታሪክ ጠላቶቻችን ተንበርክከው ይዞታችንንና ራሳችንንም ጭምር አሳልፈው ሰጥተዋል። ይህ ደግሞ የጥቃት ሁሉ የመጨረሻ ደረጃ ነው። ታሪክም ፣ ባሕልም ፣ ክብርም ያጣን ገልቱዎች እንድንሆን ተፈርዶብናል። ምርጫው የአያት-ቅድመአያቶቻችንን ጋሻ አንስቶ መከላከል ፣ የአገሪቱን ሉዓላዊነት ማስከበር ፣ ሕልውናችንን መጠበቅና እንደ ሰብአዊ ፍጡር ፣ እንደማህበረሰብ ፣ እንደኩሩ ዜጋም ታይቶ መኖር ወይም በባርነት ቀንበር መውደቅ ነው ። ሁለተኛው የምንመርጠው ምርጫ አይደለም ። ቀዳሚዎቹን ምርጫዎች በመራራ ትግልና መስዋእትነት ካላስከበርናቸው በምኞትና ፍላጎት ብቻ እውን የሚሆኑ ባለመሆናቸው በተግባራዊ እንቅስቃሴ እውን እንዲሆኑ አሁኑኑ በጋራ እንድንነሳ ወቅቱ ግድ ብሎናል።

በሰሞኑ በሳኡዲ አረቢያ በወገኖቻችን ላይ እየደረሰ ያለው ኢሰብአዊ ድርጊት በዚህ በያዝነው ሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን ማገባደጃ ላይ ይፈጸማል ተብሎ ከቶውኑ አይታሰብም። ዕብሪትና ጥጋብ አያሳየው ግፍ የለምና እያየነው ነው። በአገር ውስጥ ወያኔ/ኢህአዴግ በዜጎቻችን ላይ እያደረገ ያለው ግፍ በባእዳን ሲደገም ማየቱ ያስቆጫል ፣ ያስቆጣል፣ ከዚህ ወዲያ ምን ይመጣልም ያሰኛል ። በነፃነት ተጋድሎ የሺ ዘመናት ታሪክ ያለን ሕዝብ ፣ የቅኝ ተገዢዎች ለነበሩ የአፍሪካ ፣ የላቲን አሜሪካ---አገሮች የነፃነት ትግል አርአያና አጋር እንዳልነበርን ዛሬ በተገላቢጦሽ ራሳችንን ከጥቃት መከላከል አቅቶን መዘባበቻ ስንሆን በእጅጉ አሳፋሪ ክስተት ነው። በቅኝ ግዛት የቆዩ አገሮች እንኳ አምባገነኖችን በሕዝባዊ አመጽ ማዕበል ሲያወርዱ እኛ በአገዛዙ አፍዝ አደንግዝ ተተብትበናል። ነገሩ ሁሉ አያየዙን አይተው ጭብጦውን ቀሙት ሆኗል ወይ ነዶ ይላል የአገሬ ሰው። በሰደት የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አስተባባሪ ኮሚቴ የሳኡዲ አረቢያ መንግሥት በኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን ላይ እያፈጸመ ያለውን ኢሰብአዊ ድርጊቶች ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ደንጋጌዎችን የጣሰ የዕብሪት ጥቃት በአስቸኳይ እንዲያቆም ይጠይቃል ፤ ድርጊቱንም አጥብቆ ያወግዛል። በወገኖቻችን ላይ ለደረሰው ግድያ ፣ የአካልና የሞራል ጉዳት ፣ የንብረት መዘረፍ በደል ያደረሰው መንግሥትና የዚህ ግፍ ተባባሪ የሆነው ወያኔ በተጠያቂነት እንዲቆሙና ተበዳዮችን እንዲክሱ ከመሰል የሲቪል ማህበራትና ከሚመለከታቸው ወገኖች ጋር በመሆን ጉዳዩ ዓለም አቀፍ ገጽታ እንዲይዝና ለተግባራዊነቱም የበኩሉን ድርሻ ይወጣል።

የጭቆና አገዛዝን ለማስወገድ የኢትዮጵያ መምህራን ያላቸው የትግል ተመክሮና የከፈሉት መስዋእትነት የኢትዮጵያ የነፃነት የትግል አካል ሆኖ እስከዛሬ ቢዘልቅም የመምህራንም ሆነ ባጠቃላይ የሕዝቡ ስቃይና መከራ መቋጫ ምዕራፍ አላገኘም። እንዲያውም ሂደቱ ብዙ ትግልና መስዋእትነትን ጠያቂ እየሆነ መጥቷል። በወገኖቻችን ላይ በአረብ አገሮች የሚደርሰው አስነዋሪና አስከፊ በደል መንሴኤው አሁን በሥልጣን ያለው የወያኔ ቡድን አጀንዳና ተልዕኮ ነው። የሕዝብ ስቃይ የሚቆመው ይህ በመንግሥት ስም የተቀመጠ ቡድን በሕዝባዊ አመጽ ሲወገድ ብቻ መሆኑ አያጠያይቅም። ስለሆነም መምህራን ራሳቸውንና ህብረተሰቡን በማደራጀት ትግሉንም በመምራት የበኩላቸውን ታሪካዊ ተልእኮ እንዲወጡ ፤ ተማሪዎች፣ ወላጆች ፣ ሠራተኞች -- ባጠቃላይ መላው ህብረተሰብ በጋራ በአንድነት እንዲነሱ በስደት የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አስተባባሪ ኮሚቴ ጥሪ ያስተላልፋል።

ከተጎጂ ወገኖቻችን ጎን እንቁም!!

P.O.Box 16632 Saint Paul, MN 55116 • Tel.: 403-402-0334 • Email: eta1941@yahoo.com